# **በህጋዊ አገር ላይ የቅዠት አገር** ክፍል ፪

በአዲስ ተስፋ

ልቀጥል።ባለፉት ብዙ አመታት ሌላውን ኢትዮጵያዊ የውሸት የብሔር ብሄረሰብ ሙብት ተረጋግጧል በሚልና ማንነትን ክዶና አስክዶ የኖረ አማራ ነው በሚል ጊዜያዊ ውዥንብር ለማማለል ተሞከረ። ሁሉም የውሸት ነበር። ሶማሊያን ማን እንደሚገዛው፣ ቤንሻንጉል በማን ቁጥጥር ስር እንደሆነ፣ አፋርን ማን ቁም ስቅሉን እንደሚያሳየው፣ ጋምቤላ በማን እንደተፈጀ፣ የደቡብ ህዝቦችን ማን እንደሚያናክሳቸው፣ በአማራ ላይ ማን እንደተጫነ ፣ ኦሮሞን ታሪኩን ለማስካድ ምን ያህል እንደተሰራ አሁን ፍንትው ብሎ እየታየ ነው። ኦነግ በዚህ ሁሉ በእጅ አዙር ነበረ። **ለዐማራው አንዲት ኩርማን መሬት በሌሎች ክልሎች ልዩ ዞን ተብሎ አልተሰጠውም።** በተለይም በስፋት በሚኖርበት በመሃል አገር በምስራቅና በምእራብ ቢያንስ ቢያንስ ልዩ ዞን በተገባው ነበር። ያ ከሆነ ኢትዮጵያን የማፍረሱ እቅድ ግብ ስለማይመታ በየትኛውም መንገድ አገር ወዳዱን ህብረተሰብ ስነ ልቦናውን መግደል ዋና ተልእኮ ነበር። ዐማራው በብዛት የሚኖርባቸው **ኢሉባቦር፣ ምስራቅ ወለጋ፣ሃረርጌ፣ አሰሳ፣ መተከል፣የቀድሞው ወሎ ክፍለሃገር አፋር ክልል በተባለው እንዲሁም በከፋ አርሲና ጋሞጎፋ** የተረጋጋ ህይወት እንዳይመራ አንዴ ለቀህ ውጣ ሌላ ጊዜ ሰፋሪ እየተባለ ሲሰቃይ ኖረ። **አማርኛ ቋንቋ ሁሉም ሰው የሚግባባበት አገራዊ አንድነትን የሚያጠናክርና ኩራታችን ሆኖ እያለ ሌሎች በሃይል አማርኛን መማር እንዲያቆሙ በየትምህርት ቤሮዎች መመሪያ ተላከ።** ብቻ ጥላቻ አገር ወዳድ በሆነው ህብረተሰብ እንዲስፋፋ ሆነ። ጎጤና ነገዴ እንጂ አገሬ የሚል ዜጋ እንዲጠፋ በሰፊው ተሰራ። **ለዚህ ሁሉ መሰረቱ የህወሃትና ኦነግ ጋብቻ የሰማንያ ወረቀት የሆነው ህገ መንግስት ነው።** በአንጻሩ የሚጠላውና ተስፋፊ የሚል የጠባቦች ታፔላ የተተከለበት ይህ ዐማራ በብዛት የሚኖርበት ክልል አሁንም ሰዎች በማንነታቸው የማይገፉበት፣ እንደፈለጉ ተዝናንተውና በተሻለ መጠን ከሌላው ህብረተሰብ ጋር እኩል የሚኖሩበት ክልል ነው። እ**ስኪ የሌሎች ነገዶች ልዩ ዞን ራሱን የሚያስተዳድርበት ሌላ ክልል ኢትዮጵያ ውስጥ አለ? ከዐማራ ውጪ ማለቴ ነው**። የኦሮሚያ ልዩ ዞን፣የአዊ ልዩ ዞን ፣የዋግ ህምራ ልዩ ዞን ወዘተ ። በ1999 ዓም የህዝብና ቤቶች ቆጠራ መሰረት በዐማራ ክልል የሚኖረው **91.5%** አማራ ሲሆን ቀሪው **8.5%** ሌሎች ነገዶች ናቸው። እስኪ እግዚአብሔር ያሳያችሁ **ስምንት ነጥብ አምስት በመቶ** የሚሆነው ሌላው ነገድ ዐማራ በሚባለው ክልል ልዩ ዞን ተሰጥቶት ያለምንም ስጋት እኩል እንደሌላው ህብረተሰብ ይኖራል። ከዚህ መካከል **ኦሮሞው** ማለትም ልዩ ዞን የተሰጠው **2.62%** ብቻ ነው። በዚህም ተቃውሞ ብዙዎቻችን የለንም ። ነገር ግን ለምሳሌ በኦሮሚያ የሚኖረው **7.2%** ዐማራ ግን የልዩ ዞን ባለቤት አይደለም። ይህ ራሱ መንግስት ባደረገው የህዝብና ቤቶች ቆጠራ ላይ ተመስርቶ የተደረገ ስሌት ነው። ኦነግ የዚህ አከላለል አንዱ ኦርኬርስትሬት ስለነበረ ነው ይንን መረጃ የማቀርበው። አላማውን አገሪቱ እንድትፈርስ ያደረገው ህገ መንግስት እንዲቀጠል ከፍተኛ ልፈፋና ድጋፍ እያደረገ ያለውም ከህወሃት ቀጥሎ ኦነግ ነው። ኦነግ **ለእኩልነት ፣ለፍትህና ለእውነተኛ ዲሞክራሲ ቢታገል ኖሮ ሁላችንም ደጋፊ** በሆንን ነበር። ኢፍትሃዊ የሆነው ቋንቃንና ነገድን መሰረት ያደረገው ብቻ ሳይሆን ዐንድን የህብረተሰብ ክፍል በተናጥል የመታውን ህገ መንግስት በምን መነሻ ነው **ህጋዊ አገር ሊቀበለው የሚችለው? ለ2.62%** ኦሮሞዎች ልዩ ዞን የሰጠው ዐማራ ከየክልሎች ህዝብ ቁጠር በመቶኛ ስናሰላው በኦሮሚያ **7.2%** በሃረሪ **22.8%፣ 5.22%** በአፋር ፣ **8.4%** በጋምቤላ ፣ **21.7%** በቤንሻንጉል **0.7%**በሶማሊያ፣ **2.76%** በደቡብና ፣**20.17%** በድሬዳዋ የሚኖረው ዐማራ ባለቤት አይደለም። ለዚህ ቀመር አንደኛው ተጠያቂ ኦነግ ነው። ቢዚህ ዘረኛና ኢፍትሃዊ ፌደራሊዝም፣ ህገመንግስትና አከላለል የዐማራ ህዝብ በትእግስት ሲገዛ ኖረ። ይህም አልበቃ ብሎ ጭራሽ አዲስ አበባንና በመሳሰሉ በቆረቆራቸው ከተሞች እንዳይኖር ውጣ እየተባለ አለ። ይህንን ነው **እንግዲህ በህጋዊ አገር የቅዠት አገር ያልኩት**። ጠላቶቻችን ሊረዱትና ሊገነዘቡት የሚገባው ዛሬ ጊዜ የሰጠው ቅል ድንጋይ ይሰብራል እንደሚባለው ነገሮች የሆኑላቸው ቢመስልም ፈጽሞ የማያዋጣና ከስሩ ሊነቀል የሚገባው አረም እየተከሉ መሆኑን ነው።ለውጥ ከመጣ በመጀመሪያ ከስራ ውጪ መሆንና መታገድ ያለበት ህገ መንግስቱ ነው ስንል ፈጽሞ **ተቃራኒው ኦነግና ደጋፊዎቹ ናቸው።** የለውጥ አራማጅ የሚባሉት ዶክተር አብይም የተቀደደ ማሰሮ

ውሃ ይይዝ የመስል በሰባራው ስርዓት ጭራሽ በጥገና ልያቆዩት እየሞከሩ ይገኛሉ። **ኦነግ አመጣሁት የሚለው ድሉ ከፋፋይ የሃገሪቱ ህገመንግስት ነው። ዲሞክራሲን በባህሌና በቆየው ባህላዊ አስተዳደር ለአለም አበርክቻለሁ ከሚለው ታላቅ የኦሮሞ ህዝብ ወጣሁ የሚለው ኦነግ በዓለም ማፈሪያ የሆነ የሚለያይ፣ ዜጎችን በማንነታቸው ያገለለ ህገ መንግስት በማርቀቁ ድል ብሎ ሲጠራው መሃይምነቱን ለዓለም እያስተዋወቀ መሆኑን አልተረዳም።** ደግሞም ይህ ህገ አራዊት እያባላንና እያፋጀን እንዲቀጥል ይጥራል። የኦነግ አቋም አደናጋሪ ብቻ ሳይሆን እኩልነትንና ፍትህን ፈጽሞ አይቀበልም።ሌላም ቅዠት አለው። ለለፉት አርባ ሲደመር አመታት ህጻናት በመሬት አፈር የተለያየ ስዕል እየሳሉ እንደሚጫዎቱት ሁሉ በወረቀት ላይ ያሰፈረዉን ካርታ ይዞ ኦሮሞን እገነጥላለሁ እያለ ያላዝናል። ዶሮ ብታልም ጥሬዋን እንዲሉ ቅዠት በሆነው ህልማቸው ያዩትን ከሌላው ነገድ የጸዳች ኦሮምያን እመሰርታለሁ እያለም አፍላ ኡልበታቸውን ለልማትና ለእድገት ማዋል የሚገባቸውን ውጣቶች በጥላቻ በመሙላት ሌላውን የማግለል አላማውን ለመወጣት በመጣር ላይ ይገኛል። ከሰሞኑ በጃዋር ሙሃመድ ተሌቪዥን የተላለፈውንና ፍንፊኔን ወደ ቀደሞ ሁኔታዋ የሚል ማህበር ምስረታ ላይ የተደረገውን ውይይት መመልከቱ ለዚህ ጥላቻ አምራች ፕሮግራም አይነተኛ  ማስረጃ ነው። አዲስ አበባ ያደገች፣ አማርኛን የአፍ መፍቻዋ ያደረገች ማህበራዊ ህይዎት መለያው በሆነው ሸገር ያደገች እንዲያ ያለች ብዙ የምጸራ ወጣት በሌላው ማህበረሰብ ጥላቻ ተሞልታ እንደዚያ ስትናገር ለሰማ የኦነግን አገር አጥፊነት መረዳት ቀላል ነው። ኦነግ የተለያዩ ክንፎች አሉት፣ በመንግስት አስተዳደር ውስጥ ያሉት እነ አቶ ታይ ደንዳን የመሳሰሉት የህዝብን ገንዘብና የተሰጣቸውን ወንበር  ለእኩይ የጥላቻና ርካሽ ፖለቲካ የሚያውሉ እንዲሁም በሚዲያ ዘርፉ ያሉ እንደ ጃዋር ሙሃመድ ያሉ ደግሞ ፕሮፓጋንዳውን የሚነዙ ናቸው። ጃዋር የኦነግንና የህወሃትን አጀንዳ ሲያስፈጽም በተግባር እየታየ ሲሆን **በአፉ ለይምሰል ህውሃትን ይሰድባል።** ከሰሞኑ አንዲት አብነት ብናይ ህወሃት የማራን ህዝብ ስላም ለምንሳትና ስነ ልቦናዊ ጫና ለማድረግ ገንዘብ ከፍሎ በመቀሌ ላደራጃቸው **የቅማንንት ማንነት ተወካይ ነን ባዮች** የሰጠውን ሽፋን ማየቱ በቂ ነው። ጃዋር እነዚህን ከዛፍ ስር ተሰብስበው በሉ የተባሉትን እየተንተባተቡ የሚሉ ግዥ ሰዎች በቴሌቪዥኑ ሲያቀርብ ተመልክተነዋል። የኢትዮጵያ ህዝብ ብቻ ሳይሆን ታዛቢዎች እንኳ የህወሃትን ተንኮል ያዩበትንና የሸር ፖለቲካው ክፍል የሆነውን እጅግ የሚያስቆጣ መልእክት ማስተላለፉ አፍቃሪ የዘርና የፋይማኖት ግጭት ለሆነው ጃዋር ብቻ ሳይሆን የኦነግን ከንቱነት ያስረዳ ድርጊት ነበር። ከኦነግ ጋር በፖለቲካዉም ይሆን በሚፈልገው አቅጣጫ ፊት ለፊት መግጠም ያለብን ጊዜ ቢኖር አሁን ነው። **ዐማራና የተቀረው ኢትዮጵያዊ ሁለተኛ ዘጋ አይደለም፤** ሀገራችን ለሁላችንም ነች። ሑላችንም በእኩልነት ፣ በነጻነትና በየትኛውም የሃገራችን ማእዘን ያለመሳቀቅ ተንቀሳቅሰን መስራትና መኖር የምንችልባት አገር ልትሆን ይገባል። በዘር በቋንቋና በአድልዎ የተሞላው እያጋጨን እያጫረሰንና በስጋት እንድንኖር ያደረገው **የህወሃትና የኦነግ የሰማኒያ ወረቀት ሊቀደድ ይገባዋል።** በህጋዊ ሃገራችን በቅዠትና በጥላቻ የተመሰረተ ሌላ አገር ሊኖር አይገባውም።አበቃሁ!

ድል ለተጨቀነው ለተገፋውና ለተናቀው የሃገራችን ህዝብ እንዲሁም ባጎረስኩ ተነከስኩ ለሆነው የዐማራ ህዝብ!!!

©አዲስ ተስፋ